# ለመምረጥ ከስራ ፍቃድ ስለማግኘት

VOTE 2016

## ከደሞዝዎ ምንም ሳይቆረጥ፡ ከግል ወይም ከዓመታዊ ዕረፍትዎ ሳይቀነስ ሂዶ ለመምረጥ ፍቃድ ማግኘት መብትዎ ነው።

የሚመርጡበት ሰዓት ስራ ላይ ባሉበት ግዜ ከሆነ፡ ኣሰሪዎ ለመምረጥ ለሚያስፈልግዎ ግዜ ሊከፍሎት ይገባል። ኣሰሪዎ የግል ግዜዎን ወይም የዕረፍት ግዜዎን እንዲጠቀሙ ሊጠይቅዎ ኣይችልም።

ሂዶ ለመምረጥ የሚያስፈልጎትን ግዜ ብቻ ይውሰዱ። ከዛ በውሃላ ወደ ስራዎ ተመለሱ።

ኣሰሪዎ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መልኩ ሂደው እንዲመርጡ ሊከለክልዎ፡ ወይም በዚህ መብት ጣልቃ ሊገባ ወይም ለመመረጥ በስንት ሰዓት ላይ መሄድ እንዳለቦ ሊመርጥልዎ ኣይችልም።

ኣሰሪዎ፡ በስንት ሰዓት ላይ ከምርጫው ቦታ እንደምትመለሱ ሊጠይቅ ይችላል። በተጨማሪም ስራ የሚደናቀፍበትን ግዜ ለማሳነስ፡ ሁሉም ሰራተኞች በኣንድ ግዜ እንዳይሄዱ ሊያሳስብ ይችላል።

በማንኛውም የመላው ኣገር፡ በክፍለሃገርና ግዜው በደንብ በታወቀ በኣካባቢ ምርጫዎች ላይ ለመሳተፍ ከስራ ፍቃድ የማግኘት መብት ኣሎት።

### የ2016 ቀናት

**የማጣርያ ምርጫ**

*ማክሰኞ፡ ነሃሴ 9 ቀን*

**በኣካል ሳይገኙ የሚደረግ ምርጫ**

*በፖስታ መምረጥ ወይም በኣካል ተገኝተው የሚመረጥበት ቀን - ከመስከረም 23 ቀን እስከ ህዳር 7 ቀን*

**ለመምረጥ ተመዝገቡ**

*በዋናው ምርጫ ቀን፡ ግዜ ለመቆጠብ ቀደም ብለው በግዜ እስከ ጥቅምት 18 ቀን ለመምረጥ ይመዝገቡ።*

**የምርጫ ቀን**

*ማክሰኞ ህዳር 8 ቀን*

## ቅሬታዎች

ይህንን የምርጫ ህግ የሚያፈርስ ኣሰሪ፡ ሕግ በማፍረስ ኣነስተኛ ወንጀል ተከሳሽ ነው። ከሰራተኞች የሚነሳ ቅሬታ በቀበሌው ጠበቃ ጽሕፈት ቤት ሊመዘገብ ይገባል።

ከበስተጀርባ ይቀጥላል...

*የሚኖሶታ የኣገር ውስጥ ኣስተዳደር ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት*

mnvotes.org • 1-877-600-VOTE

# ለመምረጥ ከስራ ፍቃድ ስለማግኘት

VOTE 2016

...ከበፊቱ ገጽ የቀጠለ

## *በአካል ሳይገኙ ወይም ከዋናው የምርጫ ቀን በፊት ለመምረጥ በሚያስችል ወረቀት አስቀድሞ መምረጥ*

በዋናው የምርጫ ቀን ለመምረጥ ካልፈለጉ ወይም ካልቻሉ ከምርጫው ቀን በፊት ቀደም ብለው መምረጥ ይችላሉ። ከዓርብ መስከረም 23 ቀን ጀምሮ ወደ ምርጫ ጣብያዎ ሂደው በሞሉት ወረቀት ለመምረጥ ይችላሉ። በአካል መገኘት ለማይችሉ የሚሰጥውን የምርጫ ወረቀትም በፖስታ እንዲላክልዎ መጠየቅ ይችላሉ።

የአካባቢዎ የምርጫ ጣብያ የት እንደሆነ ለማወቅም ሆነ የ ምርጫ ወረቀት እንዲላክሎት መጠየቅ ከፈለጉ mnvotes.org.ይጎብኙ

**_ለአሰሪዎ የሚሰጥ ደብዳቤ_**
*ከስራ ወጥተው የመምረጥ መብት እንዳሎት ለአሰሪዎ የሚያስረዳና የሚሰጥ ደብዳቤ ለማግኘት mnvotes.org ይጎብኙ።*